


For Junior Doctors

# GUIDE

## On how to open a clinic or diagnostic center in Ethiopia?

**BY DR.DANIEL FENTANEH (MD)**

Lecturer at Woldia University
Founding member of DMC
Author of Debol surgery handbook
2013/2020

Happy Ethiopian New Year
New Year Gift For You
Wish You All The Best

## Contents

ምስጋና ........................................................ 3

መግቢያ ........................................................ 4

1.በጋራ ክሊኒክ/ ዲያግኖስቲክ ሴንተር ማቋቋም እንዴት ይቻላል ........................................................ 5

1.1. የጋራ ባንክ አካዉንት መክፈት ........................................................ 5

1.1.1 የብድር አማራጮች ........................................................ 6

1.2. ቃለ ጉባኤ ሳምፕል ........................................................ 7

1.3. የማህበር መመስረቻ ፅሁፍ ሳምፕል ........................................................ 8

1.3. መተዳደሪያ ደንብ አዘገጃጀት ሳምፕል ........................................................ 11

1.4. የተመረጡ የክሊኒክ እቃዎች የገቢያ ጥናት በዚህ አመት ........................................................ 14

1.4.1 ለቋሚ ንብረት ግዥ የገቢያ ጥናት በያዝነዉ አመት ........................................................ 14

1.4.2 ለመመርመሪያ ክፍል አላቂ እቃዋች ግዥ ጥናት ........................................................ 15

1.4.3. የላብራቶሪ ክፍል አላቂ እቃዋች ግዥ ጥናት ........................................................ 16

1.4.4. ከሚፈቀዱ መድኃኒቶች መካከል የግዥ ጥናት ........................................................ 17

1.4.5. ሌሎች ሊኖሩ የሚችሉ ወጮዎች ........................................................ 18

1.5. የሙያ ፈቃድ አወጣጥ ........................................................ 20

1.5.1 ቤት መከራየት እና ዉል መያዝ ........................................................ 20

1.5.2 ሙያ ፈቃድ መከራየት/ ካላችሁም ዝግጁ ማድረግ ........................................................ 21

5.3. ጤና ጽ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣችሁ በማመልከቻ መጠየቂያ ሳምፕል ........................................................ 22

1.5.4. የብቃት ማረጋገጫ ሳምፕል ........................................................ 23

1.6. የባለሙያ ቅጥር ........................................................ 24

1.7. ስራ መጀመር ........................................................ 25

1.7.1. ወጭ እና ገቢን በደንብ እየመዘገቡ መያዝ ........................................................ 25

1.8. የንግድ ፈቃድ አወጣጥ ........................................................ 28

1.9. ስለ ግብር ........................................................ 35

2.በግል ክሊኒክ/ዲያግኖስቲክ ሴንተር ማቋቋም ........................................................ 38

DEBOL
Medicine's Creativity Hub!

## ምስጋና

የከበረ ምስጋናየ ይህንን ፅሁፍ እንዳዘጋጀ ለገፋፋኝ ለዶ/ር ሳሙኤል ደረጀ (ወልድያ ሆስፒታል)፤ በተጨማሪም የደቦልን የቴሌግራም ቻናል፣ የፌስቡክ ገጽ፣ ዌብሳይት፣ የዩቲዉብ ቻናል በማስተዳደር ከጎኔ ላላችሁ ለ ዶ/ር ቢኒያም ስሜነህ (ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ) ፣ ዶ/ር አቢግያ አስቻለዉ (ከጎንደር ዩኒቨርስቲ)፣ ዶ/ር ጌታነህ ካሴ (ከፍኖተሰላም ሆስፒታል)፣ ዶ/ር ኪሩቤል ተስፋየ (ከስፔን)፣ ዶ/ር ዮናስ አ.ጥሩነህ፣ ዶ/ር ሰለሞን ታረቀኝ፣ ዶ/ር ጆቴ ልጃለም (ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ) እንዲሁም ለ Medicos Art Club መስራች ዳግማዊ ሙሉጌታ (ጅማ ዩኒቨርስቲ- ሲኒየር የህክምና ተማሪ) እና ለብሩክ መንግስት (ከኒዉዝላንድ) ይድረስልኝ።

**Telegram channel**
**t.me/Debolteam**

**YouTube channel**
https://www.youtube.com/channel/UCZ0lBTvCctutXxL462pe-RQ?app=desktop

**Facebook page**
https://www.facebook.com/deboldfp/

**Website**
**www.debolmag.com**

Medicine's Creativity Hub!

## መግቢያ

በዚህ አጭር እና ቀላል መመሪያ ዉስጥ የተጠቃለሉ የገቢያ ጥናቶች ይህ ፅሁፍ እስከተዘጋጀበት ድረስ የነበረዉን ዋጋ ታሳቢ በማድረግ የቀረበ መሆኑን ልብ እንድትሉልኝ እፈልጋለሁ። በተጨማሪም እንደ መሳሪያዎቹ ብራንድ እና የመስራት አቅም እዚህ ካቀረብኩት የገብያ ጥናት ጋር  የተጋነነ የዋጋ ልዩነት በገቢያዉ ዉስጥ ልታገኙም ትችላላችሁ። ይህም የተፈጠረዉ ትኩረቴ ጀማሪ ሐኪሞችን ባላቸዉ ትንሽ ካፒታል ወደ  ስራ እንቅስቃሴ መግባት ይችሉ ዘንድ ለአቅማቸዉ ሊመጥኑ የሚችሉትን ስላሰፈርኩ ነዉ።

ይህ ጊዜ ያልፋል። በዚህ ትዉልድ ተስፋ አለኝ። ነገሮች ይስተካከላሉ። ህክምናዉ እና ሀኪሙ ወደ ቀደመዉ ማማ ይወጣሉ። አዲስ እየመጣ ያለዉ የሀኪም ትዉልድም ለታናሾቹ መንገዱ ይጠርጋል.....

ዶ/ር ዳንኤል ፈንታነህ
ወልድያ ዩኒቨርስቲ
2013/2020

DEBOL
Medicine's Creativity Hub!

# 1.በጋራ ክሊኒክ/ ዲያግኖስቲክ ሴንተር ማቋቋም እንዴት ይቻላል

## 1.1. የጋራ ባንክ አካዉንት መክፈት

የመጀመሪያዉ፣ወሳኙ እና በማህበር ስራ ወቅት በጣም ጥንቃቄ ከሚጠይቀዉ ነገር የስራ አጋር መምረጥ ነዉ፡፡ ዛሬ የምትመርጠዉ የስራ አጋር ለድርጅታችሁ ቀጣይነት ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለዚህ ቆም ብለህ አስብ/አስቢ፡፡ በተጨማሪ  የስራዉን እና የምትሰራበትን ቦታ አዋጭነት መገምገም ይኖረብሀል፡፡

የስራ አጋር፣ የስራ ቦታ እና አዋጭነቱ ላይ ድምዳሜ ላይ ስትደርስ፤ እንዲሁም ከዚህ ፅሁፍ የምታገኘዉን መረጃ ከራስህን የገብያ ጥናት ጋር አቀናጅተህ የደረስክበትን አጠቃላይ የገንዘብ መጠን እንደየአክሲዮናችሁ ወደ ጋራ አካዉንታችሁ ገቢ አድርጉ፡፡ ገንዘቡ ከአቅማችሁ በላይ ከሆነ የምትችሉትን አቅም በማዋጣት ሌላዉን በብድር የምታገኙበትን መንገድ አፈላለልጉ፡፡ የህክምና እቃዎችን በብድር በማቅረብ ከሚሰሩ ድርጅቶች ዉስጥ ለጥቆማ ያህል ዋልያ ካፒታል ተጠቃሽ ነዉ፡፡

የጋራ አካዉንታችሁ በስራ አስኪያጁ፣ ሒሳብ ሹም እና ገንዘብ ያዥ በጣምራ መከፈት ይኖርበታል፡፡



## 1.2. ቃለ ጉባኤ ሳምፕል

**............................................... ኃላፊነቱ የተ/የግል ማህበር (የሽርክና ማህበር)**

**<u>የስብሰባ ቃለ- ጉባኤ</u>**

የስብሰባ ቦታ፡- ............................

የስብሰባ ቀን ፡-..............................

የስብሰባ ሰዓት ፡-...........................

**ተሰብሳቢዎች፣**

| ተ/ቁ | ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከተማ | ክ/ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
| 1 | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | |
| ... | | | | | | | |

አለንበት፡፡

**የስብሰባ አጀንዳዎች**

- የማህበሩን ስራ አስፈፃሚ መርጦ መሰየም
- የመመስረቻ ጽሁፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ትክክለኛነት በማየት እንዲፀድቅ ለመወሰን መሆኑን ሰብሳቢው ለአባላቱ ገልፀው አባላቱም በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በዝርዝር ተገቢውን ዉይይት ከአካሄደ በኋላ የሚከተሉት ውሳኔዎች ተወስነዋል ፡፡

**ውሳኔ**

የመጀመሪያዉ አጀንዳ፣

የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን መርጦ መሠየምን በተመለከተ አባላቱ የማህበሩን አላማ ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ያላቸዉን ከማህበሩ አባላት መካከል በከፍተኛ ዉይይት የሚከተሉትን መርጧል፡፡

ዶ/ር ...............................................................---------------ሰብሳቢ

ዶ/ር ...........................................................------------------ሒሳብ ሹም

ዶ/ር ............................................................................... ገንዘብ ያዥ ሆነዉ በአንድ ድምጽ ተመርጠዋል ፡፡

የሁለተኛውን አጀንዳ በተመለከተ፣

የእለቱ የስብሰባ መሪ ጉዳዩን በንባብ አሰምተዋል፡፡ አባላቱም የመመስረቻ ጽሁፉን እና የመተዳደሪያ ደንቡን በንባብ ከሰሙ በኋላ በእያንዳንዱ አንቀፅ እና ንዑስ አንቀፅ ላይ በሠፊዉ እየተወያዩ መግባባት ላይ ሲደርሱና ትክክለኛነቱን ሲያረጋግጡ እያንደንዱን ጉዳይ በየደረጃዉ እያፀደቅን ሂደናል፡፡ በማስከተልም የተወሰኑትን ዉሳኔዎች በፊርማችን ለማጽደቅ ሁላችንም ተስማምተን በአንድ ድምጽ በመወሰን የዕለቱ ስብሰባ ተጠናቋል ፡፡

DEBOL
Medicine's Creativity Hub!

## 1.3. የማህበር መመስረቻ ፅሁፍ ሳምፕል

**........................................................... ....................................................ማህበር**

**የመመስረቻ ፅሁፍ**

**ምስረታ**

በሰነዱ ግርጌ ፊርማቸውን ባሰፈሩት መካከል የኢትዮጵያ ንግድ ህግ በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ ተያይዞ በሚገኘው የመተዳደሪያ ደንብ ስምምነቶች የሚገዛና ዓላማውም ከዚህ በታች በአንቀጽ 4 ስር የተመለከቱትን የንግድ ስራ ተግባራት ማከናወን የሆነ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለመመስረት ስምምነት ተደርጓል ።

| ተ/ቁ | ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከተማ | ክ/ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
| 1 | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | |
| ... | | | | | | | |

***አንቀጽ አንድ***

**የማህበሩ ስምና ዋና መስሪያ ቤት**

- የማህበሩ ስም ............................................................................................ ማህበር ነው፡፡
- አባላት ወደ ፊት በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞችም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ የመክፈት መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበው የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት...........................................ማህበር.......................... ከተማ፣ ............................ ክፍለ ከተማ/ወረዳ.................ቀበሌ፣የቤት ቁጥር...................... ነው ።

**የማህበሩ የንግድ ስራ አላማዎች**

- በጤናዉ ዘርፍ ተሳትፎ በማድረግ ማለትም በፋርማሲ፣በክሊኒክ፣ ሆስፒታል እና በመሰሰሉት መሳተፍ
- በትምህርት ዘርፉ በመሳተፍ በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ ማለትም ከኬጅ እስከ ከፍተኛ ትምህርት፣አጫጭርና ረጃጅም ስልጠናወዎችን መስጠት
- ሁለገብ የገበያና የንግድ ማዕከሎችን መገንባትና ስራ ላይ እንዲዉሉ ማድረግ
- ከፍተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸዉ ዜጎች የመኖሪያ ቤት እየገነቡ ማስተላለፍ
- ጠቅላላ የንግድ ስራዎችን በመስራት ለአካባቢዉ ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት መስጠት
- በአግሮኢዱስተሪዉ ዘርፍ በመሳተፍ በአካባቢዉ የሚመረቱ የግብርና ዉጤቶችን እሴት ጨምሮ ለገበያ ማቅረብ
- በአገሪቱ ዉስጥ የሚመረቱ ምረቶችን ወደ ዉጭ በመላክና ከዉጭ የሚገቡ አስፈላጊ ምርቶችን ወደ ሀገር ዉስጥ ማስገባት
- በሆቴልና ቱሪዝም እንዲሁም በካፌና መዝናኛ ዘርፎች መሳተፍ
- የሀገሪቱን እድገት በማፋጠን ሂደት የድርሻዉን ሚና መጫዎት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

**ካፒታል**

• የማህበሩ ካፒታል ብር ............../ ........... ብር/ ሲሆን ይኸው ገንዘብ ጠቅላላ በጥሬ ገንዘብ በአባላት ተከፍሏል ፡፡ ጠቅላላ ካፒታል የእያንዳንዳቸው ብር......................... ዋጋ ባላቸው...................... ዕጣዎች ተከፍሏል ፡፡

**አንቀጽ ሁለት**

• ለመሸጥ የታሰበው የዕጣ ብዛት ................................ ሲሆን የአንዱ ዕጣ ዋጋ................................./................ብር/ጠቅላላ......................./...............ብር/ ነዉ፡፡

| | ሙሉ ስም | የእጣ ብዛት | የአንዱ እጣ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| ... | | | | |

**አንቀጽ ሶስት**

**የአባላቱ ኃላፊነት**

• ከላይ የተጠቀሰው ካፒታል በጥሬ ገንዘብ / በአይነት በሙሉ የተከፈለ መሆኑን በአንድነት እና በነጠላ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም የአባላቱ ኃላፊነት በማህበሩ ውስጥ ባላቸው ዕጣዎች መጠን የተወሰነ ነው ፡፡

**አንቀጽ አራት**

**የትርፍና ኪሳራ ክፍፍል**

• አባላቱ በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ከጠቅላላው ዓመታዊ ትርፍ ህጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብና ሌሎች ጠቅላላ ወጪዎች ከተቀነሱ በኃላ ቀሪው በአባላቱ መካከል እንደ ዕጣ ይዞታቸው ይከፋፈላል ፡፡ ሆኖም በማነኛውም ሁኔታ አባላቱ በማህበሩ ውስጥ ካላው የዕጣ ካፒታል በላይ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ፡፡

**አንቀጽ አምስት**

**ስራ አመራር**

• የማህበሩ ስራ ስልጣንና ተግባሩ በመተዳደሪያ ደንብ በዝርዝር የተመለከተ ፣ ከአባላቱ መካከል ወይም ከውጭ በአባላቱ በሚመረጥ የስልጣን ዘመን ሁለት ዓመት በሆነ እንደ ዋና ስራ አስራኪያጅ ይመራል ፡፡ በዚህ መሰረት በአቶ/ወ/ሮ/ወሪት/ዶ/ር ..................... መጀመሪያ የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆነው ተመርጠዋል ፡፡

• የዘርፍ ስራ አስኪያጆችን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ተግባራቸውን ዘርዝሮ ይሰጣል ፣ ይቆጣጠራል

• የማህበሩ ስራ አስኪያጅ የስራ ዘመናቸው ሲያልቅ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ ማህበሩ በዋና ስራ አስኪያጅ እንደአስፈላጊነቱ የሚሾሙ የዘርፍ ስራ አስኪያጆች ሊኖሩት ይችላል ፡፡

• ማህበሩን በመወከል ይፈርማል ፡፡

• ለማህበሩ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባሮች ኃላፊ ነው

• የጠቅላላ ጉባኤዎችንና የስራ አመራሩን ውሳኔዎች ስራ ላይ ያውላል ፡፡

• ለማህበሩ የሚከፈል ገንዘብ መቀበል የማህበሩ እዳዎች መክፈል ማንኛውም የሃዋላ የተስፋ የባንክ ሰነድ ማዘጋጀት በጀርባ ላይ መፈረም ማደስና እንዲሁም የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኞችን የፍርድ ሰርተፍኬቶች ወይም ማናቸውም ሰነዶች ማጽደቅና ከጀርባው መፈረም

- የማህበሩን ወኪል ወይም ሰራተኛ ይቀጥራል ፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን ፣ ደመወዝን፣ ጉርሻና ሌሎች ከመቀጠሩና ከመሰናበቱ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ይወስናል ።
- በማህበሩ ስም የባንክ ሂሳብ ከፍቶ ገንዘብ ገቢ ያደርጋል ። ሂሳቦቹን በፊርማው ያንቀሳቅሳል ።
- ለማህበሩ ንግድ በመልካም ሁኔታ መካሄድ የሚጠቀሙ ግዥዎች ሽያጭና የእነዚህን ማዘዣዎች ይወስናል ።
- ከማህበሩ ንግድ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም የንግድ ልውውጥ በተመለከተ ከሶስተኛ ወገኞች ጋር ውል ይዋዋላል ።
- በማናቸውም ፍርድ ቤት ማህበሩ ከሳሽ፣ ተከሳሽ ወይም ጣልቃ ገብ በሚሆንበት ሁሉ ማህበሩን በመወከል አስፈላጊውን ይፈፅማል ።
- ማህበርተኞች ሊቀበሉትና ሊያፅድቁት እንዲችሉ የሂሳብ ወጪና የገቢ መዝገብ በደንብ እንዲያዝ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ። የማህበሩ ዓላማ ግብ እንዲመታ አስፈላጊ መስሎ በታየው ጊዜ ከላይ ከተገለፁት ተግባራት መሃል ማናቸውንም በሌላ ሰው/ሰዎች እንዲፈፀም በማህበሩ ስም ውክልና መስጠት ይችላል ።

## አንቀጽ ስድስት

**ኦዲተር**

ማህበሩ ከአባላቱ የሚመረጡ ኦዲተር/ኦዲተሮች ይኖሩበታል ።

## አንቀጽ ሰባት

**የማህበሩ ሒሳብ አመት**

- የማህበሩ የሒሳብ የበጀት አመት ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ቀጣይ አመት ሰኔ 30 ቀን ድረስ ይሆናል ።
- የመጀመሪያ በተለየ ሁኔታ ለመወሰን ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበሩ የተቋቋመው ባልተወሰነ ጊዜ ነው

## አንቀጽ ስምንት

**የማህበሩ የስራ ዘመን**

- አባላቱ በተለየ ሁኔታ ለመወሰን ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበሩ የተቋቋመው ባልተወሰነ ጊዜ ነው።

| | ሙሉ ስም | የስራ ኃላፊነት | ስልክ | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2... | | | | |

## 1.3. መተዳደሪያ ደንብ አዘገጃጀት ሳምፕል

**................................................................. ........................................................................ማህበር**

**የመተዳደሪያ ደንብ**

### አንቀጽ አንድ

**ጠቅላላ**

- ይህ የመተዳደሪያ ደንብ የዘዉል ስሙ ............................... ማህበር የመመስረቻ ጹሁፍ የማይነጣጠል አካል ሆኖ ያገለግላል ።
- ማህበሩ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በተመለከተ በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሰረት የተቋቋመ ነው ። ስለሆነም በመመስረቻ ፅሁፉና በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ በቁጥር 510-543 የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደ አካባቢው ተፈፃሚ ይሆናል ።

### አንቀጽ ሁለት

**ካፒታል ስለመጨመር**

- የማህበሩ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ ብር ...................... (................... ብር) ሲሆን ጠቅላላ የተከፈለው ...................... (................ ብር) ነው።
- የማህበሩ አባላት ቢያንስ የካፒታሉን ¾ ድርሻ የያዙት ባለ ዕጣዎች ሲስማሙ የኩባንያውን ካፒታል ማሳደግ ይቻላል ። የማህበሩ ካፒታል ሲያደላድሉ ባለ ዕጣዎች በላቸው የዕጣ ድርሻ ይሆናል ። የካፒታል ጭማሪ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ በተፈቀደው መሰረት ይፈጸማል ።

### አንቀጽ ሦስት

**ስለ ዕጣ ዝውውር**

- ዕጣዎች በአባላት መካከል እና በሞት የተለዩ ባለ ዕጣዎች ወራሽነታቸውን ላረጋገጡ ወራሾች ሲተላለፉ የአባላትን ስምምነት መጠየቅ ሳያስፈልግ በአመራሩ ብቻ ይተላለፋል።
- ባለ ዕጣዎች በማህበሩ ያሏቸውን ዕጣዎች ከማህበሩ አባላት ውጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚችሉት ከማህበሩ አባላት 2/3ኛዉ ሲስማሙ ብቻ ነው።
- ከአባላቱ መካከል በተለያዩ ችግሮች ማህበሩን ለቆ ዕጣዎችን አስተላልፎ ከማህበሩ ለመውጣት ከፈለገ ቅድሚያ ለማህብሩ ሆኖ አባላት ላልሆኑ ግለሰቦችም አስተላልፎ መውጣት ይችላል። የሚተላለፉ ዕጣዎች ድልድልም ባለ ዕጣዎች በማህበሩ ባላቸው ዕጣ መጠን ልክ ይሆናል። ዕጣዎችን ለመቀበል የፈለጉ ከአንድ በላይ ባለ ዕጣዎች ከኖሩ ድርሻ ለሌላቸው ለሚፈልጉት ባለ ዕጣዎች በዕጣ ይዞታቸው መጠን መሠረት ይተላለፋል።
- የዕጣዎች ዝውውር / ማስተላለፍ / በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን በማህበሩ መዝገብ ካልተመዘገበ ዋጋ አይኖረውም። እንዲሁም የተፈፀመው የዕጣ ዝውውር ስልጣን ላለው መዝጋቢ አካል በመግለፅ እና አስፈላጊው ህጋዊ ሁኔታ እንዲሞላ መደረግ አለበት።
- ከላይ የተጠቀሱት ሐሳቦች እንዳሉ ሆነው ዕጣዎች የማኅበሩ አባል ላልሆነ 3ኛ ወገን ሲተላለፉ ነባር አባሉን ተክቶ የሚገባው አዲስ አባል ሙያው/የትምህርት ዝግጅቱ ሐኪም ወይም ሌላ የጤና ባለሙያ(ጤና መኮንን፣ ነርስ፣ ላብራቶሪ ባለሙያ) መሆን አለበት።

## አንቀጽ አራት

**የማህበሩ አባላት መብትና ግዴታ**

እያንዳንዱ የማህበሩ አባል

ሀ/ ማንኛውም የማህበሩ አባል ስብሰባ ላይ የመካፈል ግዴታ

ለ/ በስብሰባዎች ላይ ተገኝተዉ በያዙት ዕጣ ብዛት መጠን ድምጽ የመስጠት መብት

ሐ/ ማናቸውም የማህበሩን የወጭ እና ገቢ ሰነዶች የኦዲት ሪፖርቶች ሀብትና ሚዛን እና የሂሳብ ሪፖርት የመመርመርና መዝግቦ የመያዝ መብት፤

መ/ ለዚህ መተዳደሪያ ደንብ ለመመስረቻ ጽሁፍ እና በማህበሩ አባላት በህግ አግባብ ለሚተላለፉ ውሳኔዎች ተገዥ የመሆን ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ አምስት

**ሰብሳቢዎች**

- የማህበሩ የሂሳብ አመት በተዘጋ ቢበዛ በአራት ወራት ውስጥ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መጠራት አለበት።
- ዋና ስራ አስኪያጅ አመታዊ ማህበርተኞች ስብሰባ ከመደረጉ 15 ቀናት በፊት ለአባላት በአደራ ደብዳቤ ጥሪ ማድረግና ለውይይት የሚቀርቡ አጀንዳዎችን ምን እንደሆነ በግልፅ ማሳወቅ አለበት ።
- ኦዲተሩ ወይም ከማህበሩ ካፒታል ከግማሽ በላይ ባለሀብት የሆኑ ባለዕጣዎች በማንኛውም ጊዜ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ ጥሪ ማድረግ ይችላሉ።

## አንቀጽ ስድስት

**ያለስብሰባ ስለሚተላለፉ ውሳኔዎች**

በህግ ወይም በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ጉባኤ እንዲጠራ አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ዋና ስራ አስኪያጅ ድምጽ ሊሰጥበት የተፈለገውን ጉዳይ ለእያንዳንዱ አባል በጽሁፍ በመላክ በጉዳዩ ላይ አባላት በጽሁፍ ድምጽ እንዲሰጡ ማድረግ ይችላል ።

## አንቀጽ ሰባት

**ምልአተ ጉባኤ**

- የማህበሩ ሰብሳባ ሊካሄድ የሚችለው ከማህበሩ ካፒታል ከግማሽ በላይ ያላቸውን የሚወክሉ ማህበርተኞች በስብሰባው ላይ ሲገኙ ነው ።
- በስብሰባዎች ላይ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚቻለው በድምጽ ነው አንድ ዕጣ አንድ ድምጽ ይኖረዋል ።

## አንቀጽ ስምንት

**ስለ ዋና ስራ አስኪያጅ**

- የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ በመመስረቻ ጽሁፍ በመተዳደሪያ ደንቡ እና በጠቅላላ ጉባኤዎች በሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች መሰረት የማከናወን ስልጣን ይኖረዋል ።
- የማህበሩን አላማ ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆነ ሰራተኞችን ብዛት እና ደመወዛቸውን ይወስናል ፣ ይቆጣጠራል ከስራ ያሰናብታል ።
- በማህበሩ አባላት ጠቅላላ ጉባኤ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በስራ ላይ ያውላል ።
- ማህበሩን በመወከል በማንኛውም አይነት ደብዳቤዎች እና የሂሳብ ሰነዶች ላይ ይፈርማል ።

Medicine's Creativity Hub!

- በማህበሩ ስም የባንክ ሂሳብ ከሂሳብ ሹምና ከገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን ይከፍታል ሂሳቡንም በጋራ ያንቀሳቅሳል ፡፡
- የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሰረት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውል ይዋዋላል ፡፡
- ማህበሩ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ ማህበሩን በመወከል አስፈላጊውን ይፈፅማል ፡፡ ይከራከራል፡፡ ወይም የህግ ጠበቃ ይቀጥራል፡፡
- የማህበሩ የሂሳብ ፣ የወጪና የገቢ መዝገብ ህግ በሚፈቅደው መሰረት መደራጀቱን መያዙን ይቆጣጠራል ፡፡
- የማህበሩ ሂሳብ ከባንክ ተፈርሞ በስራ አስኪያጅ ፣ በገንዘብ ያዥና በሂሳብ ሹም ጣምራ ፊርማ ከወጣ በኋላ ገ/ያዥ ተረክቦ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋሉን ይከታተላል፡፡
- የማህበሩ አላማ ግቡን እንዲመታ አስፈላጊ መስሎ ካገኘው ስልጣኑንና ተግባሩን የሚያከናውን ተወካይ እንዲኖረው ማድረግ ይችላል ፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

**የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተለው ስልጣን ይኖረዋል**

- የዋና ስራ አስኪያጅ እና የኦዲተሮችን ሪፖርት ያፀድቃል ወይም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል ፡፡
- የማህበሩን ዋና ስራ አስኪያጅ ይሾም፣ ይሻር ብሎም ይወስናል ፡፡
- የማህበሩን አመታዊ በጀትና ዕቅድ ያፀድቃል ፡፡
- የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴና አፈፃፀም በተመለከተ ለዋና ስራ አስኪያጅ መመሪያ ይሰጣል ፡፡
- በማህበሩ ትርፍ ክፍፍል ላይ ውሳኔ ይሰጣል ፡፡
- የማህበሩ እድገትና መስፋፋት ወይም የማህበሩ ስራ አካሄድ በህግ ፣ በመተዳደሪያ ደንብ እና በመመስረቻ ጽሁፉ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል ፡፡

## አንቀጽ አስር

ስለ ማህበሩ ሂሳብ መግለጫ ህጋዊ መጠባበቂያ

- በየሂሳብ አመቱ መጨረሻ የማህበሩን ንብረት፣የሃብትና ዕዳ መግለጫ በሂሳብ ሹሙ እየተዘጋጀ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ለኦዲተሮች ይተላለፍና ኦዲተሮች ትክክለኛነቱን/ ስህተት መኖሩን ካረጋገጡት በኋላ ማህበርተኞች እንዲያውቁት ያደርጋል ፡፡
- በኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንቀጽ 539 መሰረት በየአመቱ ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ቢያንስ አምስት በመቶ እየታሰበ በመጠባበቂያ ሂሳብ ተቀማጭ ይደረጋል ፡፡ ይህ ተቀማጭ ሂሳብ የማህበሩ ካፒታል አንድ አስረኛ ሲደርስ ግዴታ መሆኑ ይቋረጣል ፡፡

Medicine's Creativity Hub!

## 1.4. የተመረጡ የክሊኒክ እቃዎች የገቢያ ጥናት በዚህ አመት

| 1.4.1 ለቋሚ ንብረት ግዥ የገቢያ ጥናት በያዝነዉ አመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥር | ንብረት | ዓይነት | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | **አጠቃላይ ዋጋ** | ምርመራ |
| 1 | **Microscope** | Binocular microscope with 100X objective additional | 1 | 19,000.00 | 19,000.00 | |
| 2 | **Ultrasound** | Portable u/s without printer | 1 | 125,000.00 | 125,000.00 | |
| 3 | **Autoclave** | Autoclave electrical 27ltr | 1 | 5600.00 | 5600.00 | |
| 4 | **Centrifuge** | 12 wholes centrifuge | 1 | 2900.00 | 2900.00 | |
| 5 | **Fridge** | | 1 | 9000.00 | 9000.00 | |
| 6 | **Couch** | Delivery bed | 1 | 4500.00 | 4500.00 | |
| 7 | **Examination bed** | | 1 | 3800.00 | 3800.00 | Locally made |
| 8 | **weight scale** | Bathroom weight scale | 1 | 950.00 | 950.00 | |
| 9 | **ባንኮኒ** | | 1 | 4800.00 | 4800.00 | Locally made |
| 10 | **አግዳሚ ወንበር** | | 1 | 1600.00 | 1600.00 | Locally made |
| 11 | **ወንበር/ስፖንጅ** | | 4 | 700.00 | 2800.00 | Locally made |
| 12 | **ወንበር/ፕላስቲክ** | | 4 | 220 | 880.00 | |
| 13 | **ጠረንጴዛ ባለኪስ** | | 2 | 2200.00 | 2200.00 | Locally made |
| 14 | **ጠረንጴዛ ካለኪስ** | | 1 | 1100.00 | 1100.00 | Locally made |
| 15 | **Bed screen** | Bed screen 3 folding | 1 | 2800.00 | 2800.00 | |
| 16 | **Patient bed** | | 1 | 2400.00 | 2400.00 | Locally made |
| 17 | **ፍራሽ** | | 2 | 700.00 | 1400.00 | |
| 18 | **IV stand** | | 1 | 600.00 | 600.00 | Locally made |
| 19 | **Minor set** | | 1 | 1225.00 | 1225.00 | |
| 20 | **MVA with cannula & speculum** | | 1 | 1795.00 | 1795.00 | |
| 21 | **Glucometer** | Blood glucose monitoring system | 1 | 450.00 | 450.00 | |
| 22 | **Hemoglobin test system** | Hemoglobin test system | 1 | 3500.00 | 3500.00 | |
| 23 | **Metallic incinerator** | | 1 | 1350.00 | 1350.00 | Locally made |
| 26 | **CBC Machine** | | 1 | 240,000.00 | 240,000.00 | |
| 27 | **Chemistry machine** | | 1 | 80,000.00 | 80,000.00 | |

ለወጪዎቻችንን ደረሰኝ ካልተቀበልን፣ መጨረሻ ላይ አመታዊ ግብር በምንከፍልበት ጊዜ ወጪዉን ማስመዝገብ አንችልም። ስለሆነም እያንዳንዷን ወጪ በደረሰኝ በስርዓት መያዝ አንርሳ።

| 1.4.2 ለመመርመሪያ ክፍል አላቂ እቃዎች ግዥ ጥናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መጀመሪያ ወር | | |
| ቁጥር | መሳሪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
| 1 | Stethoscope | 2 | 160.00 | 320.00 |
| 2 | Thermometer | 2 | 85.00 | 170.00 |
| 3 | BP cuff | 2 | 380.00 | 760.00 |
| 4 | Fetoscope | 1 | 75.00 | 75.00 |
| 5 | Tongue depressor | 01 pk | 80.00 | 80.00 |

ለወጭዎቻችንን ደረሰኝ ካልተቀበልን፣ መጨረሻ ላይ አመታዊ ግብር በምንከፍልበት ጊዜ ወጭዉን ማስመዝገብ አንችልም። ስለሆነም እያንዳንዷን ወጭ በደረሰኝ በስርዓት መያዛ አንርሳ።

## 1.4.3. የላብራቶሪ ክፍል አላቂ እቃዎች ግዥ ጥናት

| | | መጀመሪያ ወራት | | |
|---|---|---|---|---|
| ቁጥር | መሳሪያ/ ኬሚካል | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
| 1 | H.pylori stool Ag kit | 1pk | 850.00 | 850.00 |
| 2 | HIV kit | 1pk | 400.00 | 400.00 |
| 3 | HbsAG | 1pk | 250.00 | 250.00 |
| 4 | HCV | 1pk | 330.00 | 330.00 |
| 5 | VDRL | 1pk | 250.00 | 250.00 |
| 6 | BG & Rh | 1pk | 356.00 | 356.00 |
| 7 | Widal | 1btl | 195.00 | 195.00 |
| 8 | Weil-felix | 1btl | 170.00 | 170.00 |
| 9 | Urine dipstick | 1pk | 260.00 | 260.00 |
| 10 | Rheumatoid factor | 1btl | 650.00 | 650.00 |
| 11 | Microscope slides | 1pk | 120.00 | 120.00 |
| 12 | Cover slides of 100 | 1pk | 120.00 | 120.00 |
| 13 | EDTA test tube | 1pk | 260.00 | 260.00 |
| 14 | Pipette | 2 | 1550.00 | 3100.00 |
| 15 | Pipette tips | 2pk | 125.00 | 250.00 |
| 16 | 70% alcohol | 2btl | 55.00 | 110.00 |
| 17 | Geimsa | 1btl | 195.00 | 195.00 |
| 18 | $H_20_2$ | 1btl | 66.00 | 66.00 |
| 19 | Sablon | 1 | 42.00 | 42.00 |
| 20 | ESR tube | 1 | 35.00 | 35.00 |
| 21 | Urine cap | 100 | 4.50 | 450.00 |
| 22 | Examining gloves | 4 | 88.00 | 88.00 |
| 23 | Hemoglobon strip | 3Pk | 300.00 | 900.00 |
| 24 | Glucometer strip | 1Pk | 456.00 | 456.00 |
| 25 | Urine HCG | 1pk | 77.00 | 77.00 |
| 26 | Surgical glove | 1 box | 285.00 | 285.00 |
| 27 | Carbon fuschin | 1ltr | 145.00 | 145.00 |
| 28 | Methyl blue | 1ltr | 60.00 | 60.00 |
| 29 | Oil immersion | 1btl | 180.00 | 180.00 |

ለወጪዎቻችንን ደረሰኝ ካልተቀበልን፣ መጨረሻ ላይ አመታዊ ግብር በምንከፍልበት ጊዜ ወጪዉን ማስመዝገብ አንችልም። ስለሆነም እያንዳንዷን ወጭ በደረሰኝ በስርዓት መያዛ አንርሳ።

| 1.4.4. ከሚፈቀዱ መድኃኒቶች መካከል የግዥ ጥናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መጀመሪያ ወራት | | |
| ቁጥር | መድኃኒት | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
| 1 | Normal saline | 12 | 37.00 | 444.00 |
| 2 | Ringer lactate | 2 | 37.00 | 74.00 |
| 3 | Cotton | 5roll | 16.00 | 80.00 |
| 4 | Choice pill | 1 | 165.00 | 165.00 |
| 5 | Post pill | 1 | 270.00 | 270.00 |
| 6 | Salbutamol puff | 5pk | 105.00 | 525.00 |
| 7 | Adhesive Plaster | 3 | 40.00 | 120.00 |
| 8 | Diclofenac IM | 1box | 145.00 | 145.00 |
| 9 | ORS | 1pk | 110.00 | 110.00 |
| 10 | IV cannula | 2pk | 835.00 | 1670.00 |
| 11 | Gauze | 1 | 70.00 | 70.00 |
| 12 | 5ml syringe | 01box | 145.00 | 145.00 |
| 13 | 10cc syringe | 01box | 150.00 | 150.00 |
| 14 | Foley catheter | 05 | 21.00 | 105.00 |
| 15 | NG tube | 05 | 11.00 | 55.00 |
| 16 | Surgical gauze | 01 roll | 450.00 | 450.00 |
| 17 | Cat gut | 1pk | 195.00 | 195.00 |
| 18 | Surgical blades | 1pk | 550.00 | 550.00 |
| 19 | Dressing set | 1pk | 1,650.00 | 1650.00 |

ለወጪዎቻችንን ደረሰኝ ካልተቀበልን፣ መጨረሻ ላይ አመታዊ ግብር በምንከፍልበት ጊዜ ወጪዉን ማስመዝገብ አንችልም። ስለሆነም እያንዳንዷን ወጭ በደረሰኝ በስርዓት መያዝ አንርሳ።

### 1.4.5. ሌሎች ሊኖሩ የሚችሉ ወጭዎች

እነዚህ ወጭዎች እንደምትሰሩበት አካባቢ፣ እንደምትቀጥሩት ባለሙያ ዓይነት እና ብዛት እንዲሁም እንደምትጠቀሙት የማስተዋወቂያ ዘዴ ዎጋቸዉ ቢለያይም፤ ለግምታዊ ወጭ ስሌት ያግዛችሁ ዘንድ የተወሰኑ ቁጥሮችን አስቀምጨላችኃለዉ።

| ከተቀጣሪ ሰራተኞች ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ ክፍያዎች ሳምፕል | | | |
|---|---|---|---|
| | የተጣራ ደሞዝ | የስራ ግብር | ጡረታ |
| -----ወር | 8500.00 | 245.00 | 846.00 |
| -----ወር | | | |

የተቀጣሪ ሰራተኛ ደሞዝ በፔሮል መከፈል ይኖርበታል። ይህም ህጋዊ አካሄድን በመሄድ የስራ ግብር ከከፈልንበት ያወጣነዉን ወጭ ግብር በሚጣልብን ጊዜ እንደወጭ ማስመዝገብ እንድንችል ያደርገናል።

| ከቤት ኪራይ ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ ክፍያዎች ሳምፕል | | | |
|---|---|---|---|
| | የቤት ኪራይ | መብራት | ዉሃ |
| ----ወር/2013 | 6000.00 | 100 | 75 |
| ---- ወር/2013 | | | |

የቤት ኪራይ ዉል እና የኪራዩን ገንዘብ መቀበላቸዉን የሚያሳይ በፊርማ የተረጋገጠ ደብዳቤ፣ የመብራት እና ዉሃ ቢል በአግባቡ ማስቀመጥ ይኖርብናል። ይህም ህጋዊ ያወጣነዉን ወጭ ግብር በሚጣልብን ጊዜ እንደወጭ ማስመዝገብ እንድንችል ያደርገናል።

| | ተጨማሪ ሌሎች ወጭዎች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የባነር/ ማስታወቂያ | ደረሰኝ ህትመት | ካርድ፣ መድሃኒት እና ላብራቶሪ ማዘዣ ህትመት | የጽህፈት መሳሪያ | ትራንስፖርት | የመስሪያ ቤቶች ለስራ ሂደት ማስኬጃ | የሙያ ፈቃድ |
| ----ወር | 6000.00 | 1115.50 | 1500.00 | 550.02 | 1123.00 | 490.00 | 2500.00 |

ለወጭዎቻችንን ደረሰኝ እንቀበል። ለሙያ ፈቃድ ኪራይ ደሞ ገንዘቡን መዉሰዳቸዉን የተፈረመ ደብዳቤ ይኑረን። ከሌለን መጨረሻ ላይ አመታዊ ግብር በምንከፍልበት ጊዜ ወጭዉን ማስመዝገብ አንችልም።

DEBOL Medicine's Creativity Hub

## 1.5. የሙያ ፈቃድ አወጣጥ

### 1.5.1 ቤት መከራየት እና ዉል መያዝ

የቤት ኪራይ ዉል ሳምፕል





### 1.5.2 ሙያ ፈቃድ መከራየት/ ካላችሁም ዝግጁ ማድረግ

የምትጠቀሙት የሙያ ፈቃድ ለብቃት ማረጋገጫነት እንዲበቃ ከስራ መልቀቂያ ጋር አብሮ መቅረብ ይኖርበታል።

በመቀጠልም የተከራያችሁት ቤት መስፈርቱን በተወሰነ መልኩ ማሟላት ከቻለ በቀጣይ ገጽ ባቀረብኩላችሁ ማመልከቻ መሰረት የጤና ጽ/ቤቱ ባለሙያዎች በታዉን አይተዉ፣ ከሙያ ፈቃዱ ጋር አገናዝበዉ የብቃት ማረጋገጫ እንዲጧችሁ መጠየቅ ይኖርባችኋል፡

:

በዚህ ጊዜ መረዳት ያለባችሁ ነገር ቢኖር የተከራያችት ቤት የሚጎለዉ ነገር ቢኖር እንኳ እንድታስተካክሉ ተነግሯችሁ ወደ ቀጣይ ስራዎች ትሄዳላችሁ እንጅ በአንዴ ሁሉንም ነገር ምሉዕ አድርጉ እንደማትባሉ ነዉ።



ቀን 13/04/12

ለሀብሩ ወረዳ ጤና ጽ/ቤት
መርሳ

ጉዳዩ፡ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠን ስለመጠየቅ

ከላይ በጉዳዩ ላይ ለመግለፅ እንደሞከርነው እኛ "[redacted]" በሚል ስያሜ የተደራጀን 05 ጠቅላላ ሐኪሞች በ[redacted] በተከራየነው ህንፃ ውስጥ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅታችንን በማጠናቀቅ ላይ ስለሆንን የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠን እንጠይቃለን።

ከሰላምታ ጋር

1. ዶ/ር [redacted]
2. ዶ/ር
3. ዶ/ር
4. ዶ/ር
5. ዶ/ር

✓ 0912[redacted]
✓ 0913

## 1.6. የባለሙያ ቅጥር

**ቀን.........**

# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

| ተ.ቁ | ሙያ | የትምህርት ደረጃ | የስራልምድ | ብዛት | ደሞዝ | የስራቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ነርስ | ዲፕሎማ | ከ0 ዓመት በላይ | 1 | በስምምነት | ------ | COC |
| 2 | ላብራቶሪ ባለሙያ | ዲፕሎማ | | 1 | | | COC |
| 3 | እንግዳ ተቀባይ | 12ኛ ክፍል በላይ | | 1 | | | |
| 4 | ጥበቃ | ከ10ኛ ክፍል በላይ | | 1 | | | |

ተመዝጋቢዎች ይህ ማሰታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 7 በ---------በመገኘት መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር .......... ደዉለዉማናገር ይችላሉ፡፡

- **ለጤና ጽ/ቤቱ ተሟልተዉ የሚገቡ የተቀጣሪ ሰራተኞች መረጃዎች**
    - ሲ.ኦ.ሲ
    - የተሟላ የትምህርት ማስረጃ

## 1.7. ስራ መጀመር

### 1.7.1. ወጭ እና ገቢን በደንብ እየመዘገቡ መያዝ

**የወጭ መመዝገቢያ ፎርም በራሳችሁ መንገድ ማዘጋጀት፤ ለሳምፕል ያህል…**

| ደቦል የመካከለኛ ክሊኒክ አገልግሎት ኃ/የተ/የግል ማህበር |
|---|
| **ወርሃዊ የወጭ መመዝገቢያ ቅጽ** |

ወር_______________ዓ/ም________________

| | ወርሃዊ ወጭ በዝርዝር | ብር |
|---|---|---|
| 1 | የሰራተኛ አጠቃላይ የተከፈለ ደሞዝ(ከሀኪም ዉጭ) | |
| 2 | የሰራተኛ የትርፍ ሰዓት ክፍያ (ከሀኪም ዉጭ) | |
| 3 | ለሀኪም አጠቃላይ የተከፈለ ደሞዝ | |
| 4 | ለሀኪም የትርፍ ሰዓት ክፍያ | |
| 5 | አጠቃላይ የስራ ግብር በወሩ የተከፈለ | |
| 6 | ለሙያ ፈቃድ የተከፈለ | |
| 7 | ለቤት ኪራይ የተከፈለ | |
| 8 | ለመብራት እና ዉሃ የተከፈለ | |
| 9 | ለአለቁ መድኃኒቶች (በወሩ) | |
| 10 | ለአለቁ የላብራቶሪ እቃዎች | |
| 11 | ለተበላሹ እቃዎች መጠገኛ የወጣ | |
| 12 | ለአዲስ እቃ ግዢ የወጣ | |
| 13 | ሌሎች ወጭዎች (ሶፍት፣ ማፅጃ ኬሚካሎች፣ ትራንስፖርት እና ሌሎች) | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | |

Medicine's Creativity Hub!

| ማጠቃለያ | | |
|---|---|---|
| | የኢትዮጵያ ብር | ምርመራ/Remark |
| የወሩ አጠቃላይ ገቢ | | |
| የወሩ አጠቃላይ ወጭ | | |
| **የወሩ ቀሪ ገንዘብ** | | |
| ከባለፉት ወራት የቀረ ገንዘብ | | |
| **አጠቃላይ ድርጅቱ ያለዉ ቀሪ** | | |

## 1.8. የንግድ ፈቃድ አወጣጥ

ገቢዎች መሄድ (የምትሰሩበት ወረዳ)....

1. ስያሜ መምረጥ
2. ማህበሩን ህጋዊ ማስደረግ

   አስፈላጊ ነገሮች

   i. የፀደቀዉ ስያሜ
   ii. ቃለ ጉባኤ
   iii. መመስረቻ ፅሁፍ
   iv. መተዳደሪያ ደንብ
   v. የአባላት መታዎቂያ ኮፒ
3. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር

   አስፈላጊ ነገሮች

   i. የስራ አስኪያጅ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (Tin number) እና ፎቶ
   ii. የቤት ኪራይ ዉል
   iii. የፀደቀ ቃለጉባኤ፣ መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ
   iv. የድርጅታችሁ የባንክ ቡክ
4. የንግድ ፈቃድ ለማዉጣት...

   አስፈላጊ ነገሮች

   i. ከጤና ጽ/ቤት የተቀበላችሁት የብቃት ማረጋገጫ
   ii. የድርጅታችሁ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር

አለቀ።

DEBOL
Medicine's Creativity Hub!

1.ስያሜ



ቁጥር፡-ን/ም/ፈ/785/2012

ቀን፡-13/04/2012

**ለሰሜን ወሎ ዞን ን/ገ/ል/መምሪያ**

**ወልድያ**

**ጉዳዩ:-የንግድ ስም እንዲጣራልን ስለመጠየቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው **ደቦል መካከለኛ ሜዲካል ሴንተር/ ክሊኒክ / ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር** በጽ/ቤታችን የንግድ ስም እንዲጣራላቸው በቀን 13/04 /2012 ዓም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀዋል:: ሆኖም የንግድ ስሙ በሰሜን ወሎ ዞን ን/ኢ/ገ/ል/ መምሪያ ወልድያ ከተማ መጣራት እንደሚችል በተነገረን መሰረት ያቀረቧቸውን አማራጭ የንግድ ስሞች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የላክናቸው መሆኑን እያሳሰብን የተጣራው የንግድ ስም እንዲላክልን እንጠይቃለን::

1. ደቦል መካከለኛ ሜዲካል ሴንተር/ ክሊኒክ /ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
2. ሀብረት መካከለኛ ሜዲካል ሴንተር/ ክሊኒክ /ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
3. ዶክተርስ መካከለኛ ሜዲካል ሴንተር/ ክሊኒክ / ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ

ደቦል መካከለኛ ሜዲካል ሴንተር/ ክሊኒክ / ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ማሳሰቢያ

- የፈቃድ መስጫ መደብ---92124
- ቀበሌ------------ ሰሪንቃ
- የአባላት ብዛት-------05
- የስራ አስኪያጅ ስልክ ቁጥር------0912380088

አወል ሁሴን አህመድ
Awole Hussein Ahmed

የግብር ከፋይነት ምዝገባ ሰርተፍኬት



## 1.9. ስለ ግብር

1. ወርሃዊ
2. አመታዊ

1.ከሰራተኞች የሚቆረጥ ወርሃዊ የስራ ግብር

ይህ ግብር በየወሩ ለገቢዎች በሚሰጡን ፎርም መሰረት እየሞላን ገቢ ማድረግ አለብን፡፡ ይህም ለደሞዝ የከፈልነዉን አጠቃላይ ወጭ ለማዉጣታችን ማስረጃ ይሆነናል፡፡ የስራ ግብር ያልተከፈለበት የደሞዝ ወጭ እንደወጭ አይቆጠርላችሁም፡፡ በተጨማሪም ሰራተኞቻችን የስራ ልምድ በሚጠይቁበት ሰዓት ለመፃፍ ያስፈልጋል፡፡

2.አመታዊ ግብር

አመታዊ ግብር =30% የትርፋችሁን = 30% (ገቢ-ወጭ)

- የሚመዘገብላችሁ ወጭ የደረሰኝ ማስረጃ ይኖረዉ ዘንድ ግድ ነዉ፡፡

Medicine's Creativity Hub!

የንግድ ፈቃድ ካሳደሳችሁ በኃላ የስራ አካሄድ ዑደቱ በተመሳሳይ ሁኔት ሲቀጥል እናንተ ደሞ ካሳለፋችሁት አመት በተሸለ የራሳችሁን እሴት ጨምራችዉ፣ ተወዳዳሪ ሆናችሁ በተሻለ የስራ ሞራል አዲሱን የበጀት አመት ትጀምራላችሁ።

ስለአሳለፋችሁት አመት የስራ ሂደት ለመገምገም ይመቻችሁ ዘንድ አፈፃፀማችሁን ጥናታዊ በሆነ መንገድ አቅርቡ። ለሚመጣዉ የበጀት ዓመት መስተካከል ስላለባቸዉ ነገሮች በመወያየት ምክረ ሀሳቦችን አፍልቁ። የፀደቁ ምክረ ሀሳቦችን ወደ ተግባር ቀይሩ። ለምሳሌ...ከታች ያሰፈርኩላችሁ ግራፎች መሰራት ካለባቸዉ ጥቂቶቹ ሲሆኑ በነዚህ ግራፎች ላይ በመመስረት ፣ ለምን እንደዚህ ሆነ? ፣ እንዴት እናስተካክለዉ? እያላችሁ መወያየት እና የተሻለ መፍትሄዎችን ማስቀመጥ የተጓዛችሁበትን መንገድ መለስ ብላችሁ እንድትቃኙ ከማድረጉም በላይ የወደፊት ዕጣ ፈንታችሁን ብሩህ ያደርገዋል።






## 2.በግል ክሊኒክ/ዲያግኖስቲክ ሴንተር ማቋቋም

በግል ማቋቋም ከላይ የተጠቀሱትን ሂደቶች በአብዛኛዉ ይጋራል። በግል ሲሆን ግን እንደ ማህበር ምስረታ እና የመሳሰሉት ሂደቶች ስለሚቀሩ ቀለል ያለ እንዲሆን ያደርገዋል። በተጨማሪም አብዛኛዉ ሂደት በወረዳዉ የጤና ጽ/ቤት እና ገቢዎች እዛዉ ስለሚያልቅ ጥቂት ዉጣዉረዶችን ይቀንሳል።

**New Year Gift**

**From Debol**

**To You**

**መልካም አዲስ አመት።**

**አዲሱ አመት፣**

**አዲስ ተስፋ፣**

**አዲስ ስታይል፣**

**መልካሙ ሁሉ ወደናንተ ይድረስ።**

**ዶ/ር ዳንኤል ፈ.**

**Telegram channel**
**t.me/Debolteam**

**YouTube channel**
https://www.youtube.com/channel/UCZ0lBTvCctutXxL462pe-RQ?app=desktop

**Facebook page**
https://www.facebook.com/deboldfp/

**Website**
**www.debolmag.com**